# የኢህአዴግ የመተካካት ሂደትና የአዲሱ አመራር ሚና

መንግሥቱ አለማየሁ 11/20/12

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ድንገተኛ ህልፈተ ህይወት ተከትሎ ድንጋጤ እንደተፈጠረ፣ ብሔራዊ የሀዘን ሃምንታት እንደታወጀና አገርና ሕዝብ በከፍተኛ መሪር ሀዘን ውስጥ እንደሰነበትን ይታወሳል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ከሀዘኑ ጎን ለጎን የአቶ መለስን ታላቅ ራዕይ ለማስፈፀም ይቻል ዘንድ በርካታ አመርቂ ፖለቲካዊ ሁነቶች በአገራችን ተከናውነዋል፡፡ ከእነዚህ ሁነቶች መካከል አንዱ የመተካካት ሂደት ነው፡፡

የመተካካቱ ሂደት ምንም እንኳን አሁን ከቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ህልፈተ ህይወት በኋላ የተፈጠረ አዲስ ክስተት ባይሆንም በ2002 ዓ.ም በራሳቸው በአቶ መለስ ዜናዊ የሥልጣን ዘመን ተቀርፆ ወደተግባር በመቀየር ላይ ያለና በ2007 ዓ.ም ሙሉ ለሙሉ (ራሳቸው አቶ መለስን ጨምሮ) የሚተገበር ሆኖ የታቀደ የሥልጣን ሽግግር ሂደት ነው፡፡

ይህንኑ ሂደት መሠረት በማድረግ የአቶ መለስን አስደንጋጭና ድንገተኛ ህልፈት ተከትሎ የተፈጠረውን የሥልጣን ክፍተት በመሙላቱ በኩል ይኸው መሠረቱ የተጣለውን የመተካካት ሥርዓት ፍፁም ሠላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በእሳቸው እግር ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝን በቦታው ተክቷል፡፡ የአቶ መለስ ራዕይም በተያዘለት ዕቅድ ብቻ ሳይሆን የበለጠ ተጠናክሮ በመቀጠል ላይ ይገኛል፡፡ ይህ የመተካካት ሂደትም አጠቃላይ ሕዝቡን ያስደሰተ እና ዓለምን ያስደመመ ፖለቲካዊ ሁነት ሆኖም አልፏል፡፡

እዚህ ላይ መተካካትንና ስለመተካካት ሂደት ማንሳት የተፈለገበት ዐቢይና መሠረታዊ ጉዳይ ሌላ ሳይሆን የአንዳንድ "ቅን አሳቢ" ወገኖች የማያቋርጥ ሟርት ነው፡፡ ይህ ሟርት አቅጣጫው አንድ አይደለም፤ ባለብዙ አቅጣጫና ምንጮቹም ያንኑ ያህል የተለያዩና የት የለሌ ናቸው፡፡ መነሻውም የገዥውን ፓርቲ ኢህአዴግ ድርጅታዊ ባህሪ (ራሱን እያረመ፣ እየፈተሸና ከስህተቱ እየተማረ የመሄድ ባህሪይውን) ካለመረዳት የመጣ ነው፡፡

የሟርቱና ሟርተኞቹ ግዛትም ከአገር ውስጥ ተነስቶ ባህር አቋርጦ ባዕዳን ዘንድ ይደርሳል፡፡ በአጭሩ የአገር ውስጥና የውጭ "ቅን አሳቢዎቻችን"ን ሁሉ ያካትታል፡፡ ከሟርቶቹም ዋና ዋናዎቹን ብንጠቃቅስ የሚከተሉትን እናገኛለን፡፡

ከመለስ በኋላ የሚመጣ መንግሥት ያልተረጋጋና በመለስ ጫማ መሄድ የማይችል ነው፤ አሁን ያለው ሁኔታ የሥልጣን ሽኩቻ ይታይበታል፤ አገሪቷን መፈንቅለ መንግሥት ያሰጋታል፤ የብሄረሰብ ግጭት መነሳቱ ፍፁም አይቀሬ ነው፤ የህወኃት ቡድን ሥልጣንን ከእጁ ማውጣት ስለማይፈልግ በቀላሉ ለሌላ አካል /ፓርቲ/

አሳልፎ አይሰጥም፤ በአራቱ የኢህአዴግ ድርጅቶች መካከል የሥልጣን ሽኩቻ ስለሚፈጠር አገሪቷ አደጋ ላይ መውደቋ አይቀሬ ነው፤ የሥልጣን ክፍተት ይፈጠራል /ተፈጥሯል፤ ወዘተ… የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡

እነዚህ ጉዳዮች ለርዕሰ ጉዳያችን በቂ ማሳያ ይሆናሉ ብለን እናምናለን፡፡ አንዳንዶቹ ከመተካካት ሂደቱ በኋላ የሚርት - ትንበያቸው መትነን አበሳጭቷቸውም ቢሆን በተዘዋዋሪ “ብዙዎችን ግራ ያጋባና የፖለቲካ ተንታኞችን ትንበያና አቅጣጫ ሙሉ ለሙሉ ያስቀየረ አስገራሚ ሂደት” ሲሉ በመግለፅ ክስረታቸውን በይፋ አምነዋል፡፡ ይመኑ እንጂ አሁንም ሥራቸው ታጥቦ ጭቃ ይሉት ዓይነት ነው፤ ከማሚረት ወደ ኋላ አላሉምና፡፡

ለምሣሌ - ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየረጨት ያለውንና በኃይማኖት ጉዳይ ላይ ያላቸውን አቋምና አዲስ የተዋቀረው መንግሥት ሪፎርም ማድረግ ይጠበቅበታል የሚሉትን መመልከቱ እና  መመርመሩ ብቻ ይበቃል፡፡

ይህ የኃይማኖት ጉዳይ የግለሰቦችን፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችንና ልሣኖቻቸውን ብቻ ሳይሆን የሰብዓዊ መብት ተሚጋች ነን ባይ ተቋማትንም ያካትታል፡፡ ለዚህም የሰሞኑን የአምነስቲ ኢንተርናሽናልን የተለመደ የፀረ ኢትዮጵያና አተራማሽ አቋም በምሣሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ይህ ተቋም ልብ ያላለው አንድ ዐቢይ ቁም ነገር ቢኖር የጥቂት ፀረ ሠላም ኃይሎችን “መብት” ለማስከበር በማሰብ የብዙኃኑን የሙስሊም ማኅበረሰብ ማለትም ህገ መንግሥታዊ መብታቸውን በመጠቀም መሪዎቻቸውን የመረጡትን ሠላማዊ ወገኖች መብት መጨፍለቁ ነው፡፡

ወደ የመተካካከት ውጤት ወደሆነው ወደ አዲሱ ከፍተኛ የመንግሥት አመራር አካላት እንመለስ፡፡ በአሁኑ ወቅት የተተካው አዲሱ አመራር ሙሉ ሥልጣኑን ተረክቦ ኃላፊነቱን በከፍተኛ ደረጃ በመወጣት ላይ ይገኛል፡፡ አመራሩ መንግሥታዊ ኃላፊነቱን የጀመረውም በፕሬዚዳንት ግርማ ወልደጊዮርጊስ የፓርላማ የመክፈቻ ንግግር - የዓመቱ የመንግሥት ዕቅድ - ነው፡፡ ዕቅዱንም በጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ  ማብራሪያ ተጠናክሮ ለሕዝብ ይፋ በማድረግ ነው፡፡

በዚሁ ዕቅድና በተሰጠው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ አገራችን የአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን መሠረት በማድረግ አገራችን ለሚቀጥለው አንድ ዓመት የምታከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት ቀርበው፣ በጥያቄና መልስ ዳብረውና በቂ ግንዛቤ ተይዞባቸው ወደ ተግባር  ተገብቷል፡፡

በዕቅዱም  የአቶ መለስ ዜናዊ ራዕይና የልማት ዕቅድ ከምንጊዜውም በላይ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልና በዚሁ መሠረት ግሽበትን መቀነስ፣ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ መሠረተ ልማትን ማስፋፋት… ወዘተ ላይ በስፋት እንደሚሰራ በመንግሥት በኩል ቃል ተገብቷል፡፡

ይህ ብቻም አይደለም፤ በፕሬዚዳንት ግርማ በቀረበው የመክፈቻ ንግግርና በጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም በተሰጠው ማብራሪያ በአፅንኦት እንደተገለፀው፤ ምንም እንኳን አንዳንድ የሥልጣን ፍርፋሪ ፈላጊዎች

እንዳስወሩትና እንዲሆንም እንደሚፈልጉት የፖሊሲ ለውጥ እንዲኖር ቢመኙም ይህ እንደማይሆንና እንደማይታሰብ፣ በአንፃሩ በአቶ መለስ ዜናዊ የሥልጣን ዘመን የተጀመሩት ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን የመገንባትና የማጠናከር ሥራ፣ የባንዲራ ግድባችን ግንባታ (እስካሁን ባለው ክንውን 13 በመቶ ሥራው ተጠናቋል)፣ መልካም አስተዳደርን የማስፈን…ወዘተ ሥራዎች ከመቼውም በላይ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ነው፡፡ ይህም አጠቃላይ ኢትዮጵያውያን ካሳዩት ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት ጋር ተደምሮ የዕቅዱን ስኬታማነት ከወዲሁ የሚያሳይ እንዲሆን ያደርገዋል፤ አድርጎታልም፡፡

እነዚህ  ከላይ በጥቂቱ የዘረዘርናቸው ዐበይት ሕዝባዊና መንግሥታዊ ተግባራት አገራችን ከከፋ ድህነት ትወጣና እኛ ዜጎቿ በጥቂት (10 ዓመት ባልሞላ) ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እንገኝ ዘንድ የሚያስችለን የአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ አካል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህን የአገር ራዕይ፣ የሕዝብ ፅናት፣ ትጋትና እልህ አስጨራሽ የማደግና የመበልፀግ ጥረት (አንዳንዶች ስሜታዊ /ambitious/ ቢሉትም) ከመደገፍ ይልቅ በተፃራሪው በመቆም የአገሪቱንና ሕዝቦቿን ብሩህ ጉዞ ለማጨናገፍ ቀን ከሌሊት ደፋ ቀና ሲሉ እያስተዋልን ነው፡፡ ያሳዝናል፡፡

እነዚህ ወገኖች የአፍራሽና አተራማሽ እኩይ ዓላማቸውን ለማሳካት በማሰብ የተለያዩ ሥልቶችን (ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲን፤ ነፃ ሚዲያንና ኃይማኖትን)  እንደ ሽፋን በመጠቀም ሲራወጡ ውለው ያድራሉ፡፡ ምንም በሌለበት ምንም የሆነውን ዓላማቸውን በመርዛማ ምላሳቸው ያለማቋረጥ ይረጩታል፡፡ ሰሞኑን በጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ እና ሌሎች ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች ላይ ተቀነባብሮ የተሰራጨው አሳዛኝና አሳፋሪ መሠረተ ቢስ አሉባልታም ሌላው የዚሁ ፀረ አገር፣ ፀረ ልማትና ፀረ እድገት ፕሮፓጋንዳ አንዱ ማሣያ ነው፡፡

ዓለም በኢትዮጵያ ፈጣን እድገት ጉድ እያለ ባለበት በዚህ ወቅት (ከታች የገለፅነውን - የቢቢሲን ዘገባ ይመለከቷል) እነሱ ማየት ይሳናቸዋል፡፡ ራሳቸውና መሰል ብጤዎቻቸው የፃፉትን የታሪክ ድርሳን መልሰውና መላልሰው በመጥቀስ (መመሪያቸው በማድረግ) እየጠቀሱ የአደናቃፊነት ሚናቸውን ሊያሳኩ ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም፡፡ ሌላው ቀርቶ በአቶ መለስ ዜናዊ ድንገተኛ ህልፈት በጥልቅ ያዘነውን ሕዝብ “ለምን ታዝናለህ” ብቻ ሳይሆን” ተከፍሏቸው ነው”ም ብለውታል፡፡ ይህ ምን ያህል የኢትዮጵያን ሕዝብ ባህል፣ ሥነ ልቦናና ማንነት በውል ያለመረዳት ችግር ቀስፎና ጋርዶ እንደያዛቸውና ፈር ስለመልቀቃቸው  ቅርብና ግልፅ ማሣያ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በአጭሩ እንደተመለከትነው በአሁኑ ጊዜ አገራችን በጣም የተረጋጋች፣ ከደረሰባት ሀዘን ተላቃ ፊቷን ወደጀመረችው ፈጣን ልማት ያዞረችበት፣ በተደረገው የሥልጣን መተካካት አዲሱ አመራር በሰከነና በተረጋጋ ሁኔታ አገሪቱን እየመራ ያለበትና የመለስ ራዕይ እውን ይሆን ዘንድ ሁሉም ዜጋ ከመንግሥት ጎን በመቆም ጠንክሮ እየሰራ ያለበት ታሪካዊ ወቅት ላይ ትገኛለች፡፡

ምንም እንኳን ቀደም ሲል የጠቀስናቸው ከዚህ በተቃራኒ የቆሙ ሃይሎች የተያየዘውን ፈጣን የልማት ጎዞ ለማደናቀፍ ከፉኛ ቢጥሩም ሊሳካላቸው አልቻለም፡፡ ይልቁንም የቢቢሲው ወርልድ ሰርቪስ ቢዝነስ ዴይሊ ፕሮግራም ቢዝነስ ዴይሊ ስፔሺያል ንዑስ ፕሮግራም ጋዜጠኛ ጁስቲን ሮውላት በዘገባው የኢትዮጵያን ምጣኔ

ሀብት በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተምዘገዘጉ ካሉት አገራት ተርታ የሚገኝ ብቻ ሳይሆን ከአፍሪካ ግንባር ቀደሙ፣ እድገቱና ፍጥነቱ ከነብርነት አልፎ አንበሣ ደረጃ ላይ ደርሷል ብሏል፡፡

ያቺ በከፋ ድህነት ውስጥ በመኖሯ በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድ የምትታወቀው አገር - ኢትዮጵያ ዛሬ "… has been transforming itself, not into a tiger, but into an African "lion" economy." በማለት ጋዜጠኛ ጁስቲን ሮውላት በስፋት ዘግቧል፡፡ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ በዕድገት ያለተፎካካሪ በአፍሪካ ደረጃ የመሪነቱን ቦታ ይዛ ትገኛለች፡፡ ይህ ነው እንግዲህ እኛ ያስመዘገብነው ፈጣን ዕድገትና ዓለምን ያስደመመው ምጣኔ ሀብታዊ ለውጥ፡፡ ይህም ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡